የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፴፱
አዲስ አበባ – ሰኔ ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፫

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

7th Year No. 39
ADDIS ABABA - 5th July, 2001

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፵፱/፲፱፻፺፫ ዓ.ም.
ለወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ........................ ገጽ ፩ሺ፭፻፺፩

## CONTENTS

Proclamation No. 249/2001
Export Trade Duty Incentive Scheme Establishing Proclamation .......................... Page 1591

## አዋጅ ቁጥር ፪፻፵፱/፲፱፻፺፫

### የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የአገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ግኝት ከፍ ለማድረግ የወጪ ንግድ እንቅስቃሴን ማሳደግ አስፈላጊ ስለሆነ፣

ይህንን ከግብ ለማድረስ ከሚያስችሉ እርምጃዎች አንዱ የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓቶች መዘርጋት በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «ለወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር ፪፻፵፱/፲፱፻፺፫» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩· «ተመላሽ ቀረጥ» ማለት ወደውጭ ለሚላኩ ሸቀጦች ማምረቻ በሚውሉ ዕቃዎች ላይ የተከፈለው ቀረጥ ሸቀጡ ተመርቶ ወደ ውጭ በሚላክበት ጊዜ ለከፋዩ ተመላሽ የሚሆንበት ሥርዓት ሲሆን፣ በስህተት የመጡ፣ የተበላሹ፣ የጐደሉ፣ ወይም ገዥ ያጡ ዕቃዎች ወደመጡበት በሚመለሱበት ጊዜ የተከፈለውን ቀረጥ ተመላሽ ማድረግን ይጨምራል፣

## *PROCLAMATION NO. 249/2001*

### *A PROCLAMATION TO ESTABLISH EXPORT TRADE DUTY INCENTIVE SCHEME*

WHEREAS, in order to improve the foreign currency reserve of the country enhancing export trade has become necessary;

WHEREAS, among the measures that should be taken to achieve this, is to set-up export trade incentive schemes;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Export Trade Duty Incentive Scheme Establishing Proclamation No. 249/2001."

2. *Definitions*

In this Proclamation:

1) "Duty Draw-back" means a scheme by which duty paid on raw materials used in the production of commodities is refunded upon exportation of the commodity processed and shall include refund of duties paid on goods re-exported in the same condition for being not in conformity with purchase order specifications, damaged, short delivery or not in market demand;

፪· «ቀረጥ» ማለት ወደሀገር ውስጥ በሚገቡ ወይም በአገር ውስጥ በሚመረቱ ጥሬ ዕቃዎችና ሸቀጦች ላይ የሚከፈሉ ቀጥተኛ ያልሆኑ ቀረጦችና ታክሶች ናቸው፣

፫· «ወደ ውጭ መላክ» ማለት ከኢትዮጵያ ውጪ ሸቀጦችን መላክ ሲሆን ከኢትዮጵያ ውጪ ለመሄድ በተዘጋጁ ማጓጓዣዎች ላይ ሸቀጦችን መጫንን ይጨምራል፣

፬· «ሸቀጥ» ማለት ወደአገር በገባበት ሁኔታ ተመልሶ የተላከ ወይም ለውጭ ገበያ እንዲውል የተመረተ ዕቃ ሲሆን፣ ወደ ውጪ የሚላኩ ሸቀጦችን ለመያዣ ወይም ለመጠቅለያ የሚውለውን ይጨምራል።

፭· «ተመሳሳይ» ማለት በምርት ሂደት ውስጥ በአማራጭ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ጥሬ ዕቃ ነው፣

፮· «ጥሬ ዕቃ» ማለት በማምረት ወይም በመሥራት ሂደት ውስጥ ተደባልቆ ወይም ተገጣጥሞ ለውጭ ገበያ የሚውል ሸቀጥ ለማምረት የሚውል ዕቃ ሲሆን፣ ለውጭ ገበያ የሚውሉ ሸቀጦች ማሸጊያን ይጨምራል፣

፯· «ላኪ» ማለት በአገር ውስጥ የተመረቱ ዕቃዎችን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የንግድ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም ድርጅት ነው፣

፰· «አምራች» ማለት ለውጭ ገበያ የሚውሉ ሸቀጦችን አምርቶ ወደውጭ አገር የሚልክ ሰው ወይም ድርጅት ነው፣

፱· «ቫውቸር» ማለት ለውጭ ገበያ የሚውሉ ሸቀጦችን ለማምረት እንዲውሉ ወደአገር ለሚገቡ ጥሬ ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ መክፈያ እንዲውል በገንዘብ ሚኒስቴር የሚታተም የገንዘብ ዋጋ ያለው ሰነድ ነው፣

፲· «የግብአት ምርት ጥመርታ» ማለት በተወሰነ መለኪያ አንድ የወጪ ምርት ለማምረት የሚያስፈልገውን የግብአት መጠን የሚያሳይ ነው።

፫· <u>የአዋጁ ተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ ተፈጻሚ የሚሆነው፣

፩· ቀረጥ ተከፍሎባቸው ከገቡ በኋላ አስመጪው በሚረከብበት ጊዜ የተሳሳቱ፣ የጐደሉ ወይም የተበላሹ እንዲሁም በአገር ውስጥ ገዥ ያጡ መሆናቸው በመረጋገጡ ወደመጡበት ለሚመለሱ ዕቃዎችና ሸቀጦች፣

፪· ለውጭ ገበያ ለሚውሉ ሸቀጦች ማምረቻ ወደ አገር ለሚገቡ ወይም በአገር ውስጥ ለሚመረቱ ጥሬ ዕቃዎች፣

፫· ለውጭ ገበያ ለሚውሉ ሸቀጦች መያዣ ወይም መጠቅለያ የሚያገለግሉ ዕቃዎች፣

፬· ምርታቸውን ሙሉ በሙሉ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የተቋቋሙ ድርጅቶች በቀጥታ በማምረት ተግባር ላይ እንዲውሉ ወደ አገር ለሚያስገቧቸው ዘይቶች፣ ቅባቶችና ሌሎች ኃይል ሰጪ ንጥረ ነገሮች ነው።

፬· <u>የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓቶች</u>

የሚከተሉት የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓቶች በዚህ አዋጅ በሥራ ላይ ይውላሉ፣

ሀ) የተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት፣
ለ) የቫውቸር ሥርዓት፣ እና
ሐ) የማምረቻ መጋዘኖች ሥርዓት።

<u>ክፍል ፩</u>
<u>የተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት</u>

፭· <u>የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች</u>

የተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚችሉት ፣

፩· ምርታቸውን ሙሉ በሙሉ፣ በከፊል፣ ወይም በተወሰነ ወቅት ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ አምራቾች ፣

፪· በላኪነት ንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩ፣

2) ''Duty'' means all indirect taxes and duties paid on raw-materials and commodities imported or produced locally;

3) ''Export'' means sending commodities to a place outside Ethiopia, and includes the loading of the same on a carrier proceeding to a foreign port;

4) ''Commodity'' means goods re-exported in the same condition or goods produced for foreign market and shall include goods used for packing and containing export trade commodities;

5) ''Equivalent'' means raw materials that can be used interchangeably in a manufacturing process;

6) ''Raw material'' means goods that are mixed with or fixed to other goods in the production process to bring about commodities for export, and includes goods to be used for packing and containing export commodities;

7) "Exporter'' means a person or organization licensed to engage in supplying locally produced commodities to foreign market;

8) ''Producer'' means a person or organization engaged in producing and supplying commodities to foreign market;

9) ''Voucher'' means a document having monetary value, printed by the Ministry of Finance, to be used as deposit for duties and taxes payable on imported raw materials;

10) ''Input Output Coefficient'' means a specified measurement for the use of an input to produce one unit of output.

3. *Scope*

This Proclamation shall apply to:

1) Raw-materials and commodities re-exported after having been imported upon payment of duties for being not inconformity with purchase order specifications, damaged, or not in market demand;

2) Raw-materials imported or produced locally to be used in production of export commodities;

3) Goods to be used for packing and containing export commodities;

4) Oil, lubricants, and other energy generating substance used by producers which are wholly engaged in manufacturing commodities for export.

4. *Duty Incentive Schemes*

The following duty incentive schemes are established by this Proclamation:

(a) Duty Draw-Back Scheme;
(b) Voucher Scheme;
(c) Bonded Manufacturing Warehouse Scheme.

*Section 1*
*Duty Draw–Back Scheme*

5. *Beneficiaries of the Scheme*

Persons or Organizations:

1) wholly, partially or occasionally engaged in exporting their products;

2) engaged in export trade;

፫· ቀረጥ ከፍለው ያስገቡት ሸቀጥ ወይም ጥሬ ዕቃ የተሳሳተ ፣ የተበላሸ ፣ የጐደለ፣ ወይም ገገር ያጣ በመሆኑ ምክንያት ወደመጣበት አገር መልሰው የሚልኩ፤
ሰዎች ወይም ድርጅቶች ናቸው።

፬· ከዚህ በላይ የተደነገገው ቢኖርም ምርታቸውን በከፊል ወይም በተወሰነ ወቅት ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ ሰዎች ወይም ድርጅቶች ወደ አገር የሚያስገቧቸው ጥሬ ዕቃዎች በዋጋም በጥራትም ተመሳሳያቸው በአገር ውስጥ የሚመረት ሲሆን በዚህ አዋጅ የተቋቋመው መብት ተጠቃሚ አይሆኑም። ስለሆነም የዚህ ንዑስ አንቀጽ አፈጻጸም የገንዘብ ሚኒስትሩ በሚያወጣው ዝርዝር መመሪያ ይወሰናል።

፮· ቀረጥን ተመላሽ ስለማድረግ

፩· ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፭ የተመለከቱት የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች በሚያስመጡት ዕቃ ላይ በጉምሩክ መግቢያ በሮች እንዲሁም በአገር ውስጥ የተከፈለው ቀረጥ በዚህ አዋጅ ስለተመላሽ ቀረጥ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ለመብቱ ተጠቃሚ ይመለሳል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ቢኖርም ፣ የተከፈለው ቀረጥ ልክ ከብር ፩ሺ (አንድ ሺህ ብር) በታች ለሆነው ጥሬ ዕቃ ወይም ሸቀጥ የተከፈለው ቀረጥ አይመለስም።

፫· በዚህ አዋጅ መሠረት ተመላሽ ሊደረግ የሚገባውን ቀረጥ ለመብቱ ተጠቃሚ የሚከፍለው የገንዘብ ሚኒስቴር ነው።

፬· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ክፍያው በታሳቢ ከተፈፀመ በኋላ ተመላሽ የተደረገው ቀረጥ በክልል ግብር ሰብሳቢ አካላት የተሰበሰበ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ይኸው በሚመለከተው አካል ለገንዘብ ሚኒስቴር መተካት አለበት።

፯· የተመላሽ ቀረጥ ልክ

፩· የተከፈለው ቀረጥ የሚመለስበት ሸቀጥ ወይም ጥሬ ዕቃ ወደ ውጭ አገር መላኩ ሲረጋገጥ፣

ሀ) በምርት ሂደት ውስጥ ሳያልፍ በመጣበት ሁኔታ ተመልሶ የሚላክ ሲሆን የተከፈለው ቀረጥ ፺፭ ፐርሰንት (ዘጠና አምስት በመቶ)፣

ለ) የሚላከው በአገር ውስጥ ከተመረተ ወይም ለመያዥና ለመጠቅለያነት ከዋለ በኋላ ሲሆን የተከፈለው ቀረጥ ፻ፐርሰንት (መቶ በመቶ)፤

ተመላሽ ይደረጋል።

፪· የጉምሩክ ባለሥልጣን በአገር ውስጥ ከተመረተ በኋላ ለውጭ ገበያ ለሚላከው ለእያንዳንዱ ሸቀጥ ተመላሽ የሚሆነውን የቀረጥና ታክስ መጠን ስሌት ከላኪው የባንክ ሂሣብ ቁጥር ጋር አያይዞ ለገንዘብ ሚኒስቴር ይልካል።

፰· የተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች

፩· ጥሬ ዕቃው ወደ አገር ከገባበት ወይም ከአገር ውስጥ ከተገዛበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ዓመት ውስጥ በዚህ ጥሬ ዕቃ የተመረተው ሸቀጥ ወደ ውጭ መላክ አለበት።

፪· የተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት ተጠቃሚ መሆን የሚችለው ሰው ወይም ድርጅት ጥሬ ዕቃውን ወይም ሸቀጡን ወደውጭ ከመላኩ በፊት ለመላክ መዘጋጀቱን እና የተመላሽ ቀረጥ ጥያቄ የሚያቀርብ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ ከደጋፊ ሰነዶች ጋር በማያያዝ ለጉምሩክ ባለሥልጣን ያቀርባል። የሚቀርበው ማስታወቂያ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፣

ሀ) የጠያቂውን ስምና አድራሻ፣

ለ) ጥሬ ዕቃው ወይም ሸቀጡ ከውጭ አገር የመጣ ከሆነ ወደአገር የገባበትን ጊዜ፣ ወደ አገር የገባባቸውን ሰነዶች፣

ሐ) የተከፈለውን ቀረጥ ልክ የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣

መ) ተመላሽ ቀረጥ የሚጠየቅበትን ጥሬ ዕቃ ወይም ሸቀጥ ዓይነትና ብዛት፣

ሠ) የግብአት ምርት ጥመርታ፤

3) re-exporting commodities, or raw materials, they have imported upon payment of duties, for being not in conformity with purchase specifications, damaged, short delivered or not in market demand;

4) Notwithstanding the provision laid-down above, persons or organizations partially or occasionally engaged in exporting their products shall not be beneficiaries of the schemes established by this Proclamation, where raw-materials equivalent in price and quality to those they imported are locally available. Directives to be issued by the Minister of Finance shall regulate the implementation of this Sub-Article.

6. *Duty Draw-Back*

1) Duties paid at the port of entry and locally, on goods imported by the beneficiaries indicated under Article 5 above shall be refunded to the beneficiaries of the scheme upon fulfillment of conditions laid-down in this Proclamation with respect to duty draw-back.

2) Notwithstanding the provisions laid-down under Sub-Article (1) of this Article, duties paid on commodities or raw-materials shall not be refunded where the amount of duty paid is less than birr 1000 (one thousand Birr).

3) The duty to be drawn-back in accordance with this Proclamation shall be paid to the beneficiary by the Ministry of Finance.

4) Where, part of the payment effected in accordance with Sub-Article (3) of this Article had been collected by the revenue authorities of the Regional Governments, such payment shall be reimbursed to the Ministry of Finance by the relevant body.

7. *Duty Draw-Back Rate*

1) When the export of raw material or commodity on which duty to be drawn-back is ascertained:

(a) if re-exported in the same condition 95% (ninety five percent);

(b) if exported after being processed or used for packing containing 100% (one hundred percent)

of the duty paid shall be refunded.

2) The Customs Authority shall transfer to the Ministry of Finance the amount of the tax and duty to be drawn back on each commodity exported after having been domestically produced, together with the Bank Account Number of the beneficiary.

8. *Conditions to be Fulfilled in Order to Become the Beneficiary of the Duty Draw-Back Scheme*

1) The commodity produced with the raw material should be exported within one year from the date on which such raw material has been imported or purchased locally;

2) The beneficiary of the Draw-Back Scheme shall, before exporting the commodity or raw material, declare to the Authority upon presentation of supporting documents that he is prepared to export and that he intends to claim draw-back. The declaration presented shall include the following:

(a) the name and address of the claimant;

(b) if the raw material or commodity is imported, the date of importation and the import transaction documents;

(c) the document proving the amount of duty paid;

(d) the type and quantity of the commodity or raw material on which draw-back is claimed;

ረ) ወደ ውጭ የሚላከውን ሸቀጥ ዓይነትና ስለአላላኩ ዝርዝር መግለጫ፣

ሰ) ሸቀጡ ወይም ጥሬ ዕቃው በመጣበት አኳኋን የሚመለስ ከሆነ ያለመመለሱ የሚያስከትለውን ጉዳት።

፫· የተጠየቀው ቀረጥና ቀረጡ ተመላሽ እንዲደረግ ጥያቄ የቀረበበት ጥሬ ዕቃ ወይም ሸቀጥ መጠንና ዓይነት በዚህ አዋጅ የተመለከተውን የሚያሟላ ስለመሆኑ የማረጋገጥ ኃላፊነት የተመላሽ ቀረጥ ጠያቂው ነው። ጠያቂው ይህንን በበቂ ሁኔታ ማረጋገጥ ያልቻለ እንደሆነ ጉምሩክ ባለሥልጣን የራሱን ውሳኔ የመስጠት መብት ይኖረዋል።

፬· የቀረበው የተመላሽ ቀረጥ ጥያቄ ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ የጉምሩክ ባለሥልጣን ለሚያካሂደው ምርመራ የተመላሽ ቀረጥ ጠያቂው ተገቢውን እገዛ ማድረግ አለበት።

## ክፍል ፪
## የቫውቸር ሥርዓት

፱· የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች

በቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚችሉት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሥርዓቱ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው ሰዎች ወይም ድርጅቶች ብቻ ናቸው።

፲· የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፣

በቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚችሉት የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያሟሉ ናቸው፣

፩· በአምራችነት ፈቃድ ያላቸው፣

፪· በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የንግድ ሥራ እና የወጪ ንግድ ዕቅድ የሚያቀርቡ፣

፫· የግብዓት ምርት ጥመርታ ማቅረብ የሚችሉ፣

፬· በዓመቱ የምርት ሂደት ውስጥ የሚባክነውን ጥሬ ዕቃ መጠን የሚያቀርቡ፣

፭· ለወጭ ንግድ አዲስ ካልሆኑ ያለፉትን ሁለት ዓመታት የኤክስፖርት አፈጻጸም የሚያቀርቡ ፣

፮· በቫውቸር ሥርዓት ለመጠቀም የሚያስችሉ ግዴታዎችን ለመፈፀም ከጉምሩክ ባለሥልጣን ጋር ውል የሚፈርሙ ፣

፯· ጥሬ ዕቃዎችን አቅራቢዎች በሚሰጡት ዱቤ፣ ወይም በፍራንኮቫሉታ የሚያስገቡ ከሆነ ፣

ሀ) ተፈላጊው ምርት በአገር ውስጥ ከተመረተ በኋላ የምርቱ ተቀባይ መኖሩን የሚያረጋግጥ ከገዢው የተላከ ትዕዛዝ ወይም ከገዢው ጋር የተደረገ ውል ማቅረብ የሚችሉ ፣ እና

ለ) ጥሬ ዕቃው ውጭ አገር ከሚገኝ ኩባንያ አገር ውስጥ ለሚገኝ ተባባሪ ኩባንያ የወጪ ምርቶችን ለማምረት የተላከ ከሆነ ፣ የሁለቱን ኩባንያዎች ግንኙነት የሚገልፅ ሕጋዊ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ ፣

፰· አምራቾቹ በዘርፉ ለመሠማራት አዲስ ከሆኑ ፣

ሀ) የዓመቱን የኤክስፖርት ዕቅድ ማቅረብ የሚችሉ ፣

ለ) አግባብ ካለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተሰጠ የኢንቬስትመንት የምስክር ወረቀት ወይም/እና የአምራች የንግድ ፈቃድ ማቅረብ የሚችሉ ናቸው።

፲፩· የቫውቸር ሥርዓት አፈጻጸም

፩· የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚፈልጉ አምራቾች ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፲ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች አሟልተው ሲቀርቡ ወደአገር በሚያስገቧቸው ጥሬ ዕቃዎች ላይ ሊከፈል በሚገባው የቀረጥና ታክስ ልክ የጉምሩክ ባለሥልጣን ቫውቸር ይሰጣቸዋል ።

(e) input output coefficient;

(f) the type and the detailed description of the manner of exportation of the commodity to be exported:

(g) if the commodity or raw material is re-exported in the same condition, the damage that could be caused by not being re-exported.

3) The burden of proof that the duty claimed and the raw material and commodity presented that for draw back are in accordance with this Proclamation shall rest with the claimant of the drawback, failing which the Customs Authority shall have the discretion to make its own decisions.

4) The claimant shall give all assistance to the Customs Authority while it conducts inspection to prove the accuracy of duty drawback claim.

## *Section 2*
## *Voucher Scheme*

*9. Beneficiaries of the Scheme*

Beneficiaries of the Voucher Sheme are persons and organizations who have obtained eligibility certificate issued by the Ministry of Trade and Industry.

*10. Conditions to be Fulfilled to become Beneficiary of the Voucher Scheme*

To become beneficiaries of the scheme persons and organizations must:

1) have manufacturing license;
2) submit at the beginning of the budget year their annual business and export plan;
3) submit input-output coefficient;
4) supply information concerning raw materials wasted in the process of production;
5) submit evidence of export performance in the last two years, if they are not new to the sector;
6) sign an agreement with the Customs Authority undertaking to fulfill obligations enabling them to become beneficiaries of the Scheme;
7) If the raw materials are imported on supliers credit or Franco-valuta basis:
   (a) submit evidence confirming that the commodity has demand and that the demand is confirmed by a purchase order issued by the prospective buyer or submit a purchase agreement concluded with the prospective buyer;
   (b) if the raw material is sent by a foreign company to its local affiliate with the objective of producing export commodities submit memorandum describing the mode of affiliation between the two companies.
8) If the exporters are new entries into the sector:
   (a) submit their annual export plan; and
   (b) submit an investment certificate and/or trade license from the appropriate government organ.

*11. Procedures for the Application of Voucher Scheme*

1) The Customs Authority shall issue vouchers, in the amount of taxes and duties to be paid on raw materials they may import, to producers who are eligible to become beneficiaries upon satisfying the conditions laid down under Article 10.

፪· ወደአገር የሚገቡት ጥሬ ዕቃዎች የጉምሩክ ወደብ ሲደርሱ አምራቾች የተሰጣቸውን ቫውቸር ሊከፈል በሚገባው ቀረጥና ታክስ ልክ ለጉምሩክ ባለሥልጣን እያስያዙ ጥሬ ዕቃዎቹ በቀጥታ ወደማምረቻ ቦታው የግል መጋዘን እንዲተላለፉ ይደረጋል ።

፫· የጉምሩክ የዕቃ ፍተሻ ሥርዓት የሚካሔደው በአምራቹ የግል መጋዘን ውስጥ ይሆናል ።

፬· በቫውቸር ሥርዓት አማካኝነት ወደአገር የገቡ ጥሬ ዕቃዎች ለአገር ውስጥ ገበያ ሊውሉ አይችሉም ። አምራቹ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ውስጥ የተደነገገውን ክልከላ በመተላለፍ በቫውቸር ሥርዓት ወደአገር ያስገባ ቸውን ጥሬ ዕቃዎች ሸጦ የተገኘ እንደሆነ በቫውቸር የመጠቀም መብቱን ያጣል ።

፭· ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፬) የተደነገገው ቢኖርም ፣ አምራቹ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የመላክ ንግድ ሥራውን ያቋረጠ እንደሆነ የጉምሩክ ባለሥልጣንን በማስፈቀድ ቀረጥና ታክሱን ከነወለዱ ከፍሎ ጥሬ ዕቃውን መሸጥ ይችላል ።

፮· በቫውቸር ሥርዓት አማካኝነት ወደ አገር በገቡ ጥሬ ዕቃዎች ተመርተው ወደውጭ አገር የሚላኩ ምርቶች የጉምሩክ ባለሥልጣን ለዚሁ ሲባል በሚያዘጋጀው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ኮድ መሠረት ማስታወቂያ እየቀረበባቸው ወደ ውጭ አገር ይላካሉ ።

፯· በቫውቸር ሥርዓት ወደአገር የገባ ጥሬ ዕቃ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ጥቅም ላይ መዋል አለበት ። ሆኖም የጉምሩክ ባለሥልጣን የጥሬ ዕቃውን ባህርይ መሠረት በማድረግ ይህ የጊዜ ገደብ ለተጨማሪ አንድ ዓመት እንዲራዘም ሊፈቅድ ይችላል ።

፰· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲(፫) መሠረት አምራቹ የሚያቀርበው የግብአት ምርት ጥመርታ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተገምግሞ ተቀባይነት ካገኘ የጉምሩክ ባለሥልጣን ይህንኑ ጥመርታ መሠረት በማድረግ በቫውቸር ዋስትናነት ወደአገር የገባውን ጥሬ ዕቃ የቀረጥ ስሌት ያከናውናል ፣ በስሌቱም መሠረት የተያዘውን ቫውቸር ያወራርዳል ።

፱· የጉምሩክ ባለሥልጣን ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፰) መሠረት ስሌቱን የሚሰራው ጥሬ ዕቃው ወደአገር ውስጥ በገባ ወይም በአገር ውስጥ ከተገዛበት ከ፲፩ኛው ወር የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ሲሆን ፣ ስሌቱ በ፴ ቀናት ውስጥ መጠናቀቅ አለበት ።

፲· በስሌቱ መሠረት ወደአገር ከገባው ጥሬ ዕቃ ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋለ የተገኘ እንደሆነ የጊዜ ገደቡ በንዑስ አንቀጽ (፯) መሠረት ካልተራዘመ በስተቀር አምራቹ በዚህ ጥሬ ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ እስከነወለዱ እንዲከፍል ይደረጋል ።

፲፩· የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚዎች የወጪ ምርቱን ለማምረት ከአገር ውስጥ በሚገዙት ጥሬ ዕቃ ላይ የተከፈለውን ቀረጥና ታክስ ተመላሽ ማድረግ የሚያስችለው ስሌት በጉምሩክ ባለሥልጣን ይከናወናል ። የገንዘብ ሚኒስቴር ከጉምሩክ ባለሥልጣን በሚደርሰው መረጃ መሠረት ቀረጥና ታክሱን ተመላሽ ያደርጋል ።

፲፪· የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲(፫) መሠረት ከሚያቀርቡት የግብአት ምርት ጥመርታ በተጨማሪ በታቀደው የዓመቱ ምርት ሂደት ውስጥ የሚባክነውን ጥሬ ዕቃ መጠን ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ወይም በአገር ውስጥ ገበያ የሚሸጠውን የተረፈ ምርት ዓይነት ፣ መጠን፣ በተረፈ ምርቱ ውስጥ ከውጭ አገር የገቡ ጥሬ ዕቃዎች መጠንና ዋጋ ድርሻ በመቶኛ የሚያሳይ መግለጫ ያቀርባሉ ።

2) On arrival of the imported raw materials at the Customs post, the raw materials shall directly be transferred to the private warehouse in the premises of the production site after the exporter has deposited with the Customs Authority the vouchers in the amount of taxes and duties to be paid.

3) Customs formalities shall be carried out in the producers private warehouse.

4) Raw material imported under the Voucher Scheme may not be sold in the local market. Any producer who, in violation of the prohibitions provided herein, sells the raw materials imported under the Voucher Scheme, shall forfeit his right to use the Scheme.

5) Notwithstanding the provisions of Sub-Article (4) above, if the producer, because of events beyond his control, has terminated his export activity, shall, after securing the consent of the Customs Authority, sell the raw materials upon payment of duties and taxes together with interest thereon.

6) Export Commodities produced from raw materials imported under the Voucher Scheme shall be declared and exported in accordance with Customs Procedure Code issued for this purpose by the Customs Authority.

7) Raw materials imported under the Voucher Scheme must be fully utilized within one year from the date of their importation. However, taking into consideration the nature of the raw material, the Customs Authority may extend this period for an additional one year.

8) If the Ministry of Trade and Industry accepts the input output coefficient submitted by the producer in accordance with Article 10(3), the Customs Authority shall assess the taxes and duties payable on the raw materials imported under the Voucher Scheme on the basis of this input output coefficient and settle the voucher on the basis of such assessment.

9) The Customs Authority shall commence the assessment referred under Sub-Article (8) above on the first day of the eleventh month from the date on which the raw material is imported or purchased locally, and the assessment must be completed within thirty days.

10) If raw material remains unutilized from what has been assessed, unless the period in which the raw material must be utilized is extended in accordance with Sub- Article (7), the producer shall be made to pay the taxes and duties on such raw materials together with the interest thereon.

11) The Customs Authority shall carry out an assessment of taxes and duties, paid by beneficiaries of the Voucher Scheme on raw-materials purchased locally to be used for producing export commodities, on the basis of which refund shall be made. The Ministry of Finance shall on the basis of the assessment refund the taxes and duties so paid.

12) Beneficiaries of the Voucher Scheme, in addition to input output coefficient submitted in accordance with Article 10(3), shall submit a memorandum showing the amount of raw material wasted in the course of production process, the amount and type of by-product to be supplied to a foreign or local market, the input used out of the raw material imported in the production of the by-product, in percentage, during the execution of the annual production plan.

፲፪· ቫውቸር

፩· የጉምሩክ ባለሥልጣን ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚላክለት የወጪ ንግድ ዕቅድ መሠረት የሚታተመውን ቫውቸር ልክ ለገንዘብ ሚኒስቴር ያስታውቃል።

፪· የገንዘብ ሚኒስቴር ከጉምሩክ ባለሥልጣን በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚችሉ አምራቾች ወደአገር በሚያስገቧቸው ጥሬ ዕቃዎች ላይ ሊከፈል ለሚገባው ቀረጥና ታክስ ዋስትና እንዲሆን የሚያሲዙት ቫውቸር ያሳትማል።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚታተሙት ቫውቸሮች፣

ሀ) የገንዘብ ዋጋ ያላቸው ይሆናሉ፣

ለ) ከተፈቀደለት ባለመብት በስተቀር ለሌላ ወገን በማይተላለፍ መልኩ ይዘጋጃሉ፣

ሐ) ለዋስትና አሰጣጡ በሚያመች መንገድ በባለ ብር ፻ ፡ ብር ፶ ፡ ብር ፲ ፡ ብር ፭ እና ብር ፩ የገንዘብ መጠን የሚታተሙ ይሆናል።

## ክፍል ፫

## የማምረቻ መጋዘኖች ሥርዓት

፲፫· የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች

በማምረቻ መጋዘኖች ሥርዓት መጠቀም የሚችሉት ምርታቸውን ሙሉ በሙሉ ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ፣ የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ያልሆኑ እና የፈቃድ ወረቀት የተሰጣቸው የማምረቻ መጋዘኖች ያሏቸው አምራቾች ናቸው።

፲፬· የማምረቻ መጋዘኖች ተጠቃሚ ለመሆን መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

የማምረቻ መጋዘኖች ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚችሉት የሚከተሉትን ሁኔታዎች ያሟሉ ናቸው፣

፩· የአምራችነት ፈቃድ ያላቸው፣

፪· በጉምሩክ ሕግ የተወሰነውን መስፈርት ያሟላ መጋዘን በማምረቻ ፋብሪካቸው ቅጥር ግቢ ውስጥ ያላቸው፣

፫· ለመጋዘን ፈቃድ ማደሻ እንዲሁም በመጋዘኑ ለሚመደበው የጉምሩክ ሠራተኛ በሕግ የተወሰነውን አበል የሚከፍሉ፣

፬· ለመጋዘኑ የመድን ዋስትና መግባታቸውን የሚያሳይ መረጃ የሚያቀርቡ፣

፭· በዓመት ውስጥ አምርተው ለውጭ ገበያ የሚልኩትን የምርት ዓይነት፣ መጠንና ዋጋ እንዲሁም ይህንን ምርት ለማምረት ከውጭ አገር የሚያስገቧቸውን ጥሬ ዕቃዎች የሚዘረዝር የኤክስፖርት ዕቅድ ለጉምሩክ ባለሥልጣን ማቅረብ የሚችሉ፣

፮· የግብዓት ምርት ጥመርታ ማቅረብ የሚችሉ፣

፯· ከግብዓት ምርት ጥመርታ በተጨማሪ በታቀደው የዓመቱ ምርት ሂደት ውስጥ የሚባክነውን የጥሬ ዕቃ መጠን፣ ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ወይም በአገር ውስጥ ገበያ የሚሸጥ የተረፈ ምርት ዓይነት፣ መጠን፣ በተረፈ ምርቱ ውስጥ ከውጭ አገር የገቡ ጥሬ ዕቃዎች መጠንና ዋጋ ድርሻ በመቶኛ የሚያሳይ መግለጫ የሚያቀርቡ፣ መሆን አለባቸው።

፲፭· የማምረቻ መጋዘኖች ሥርዓት አፈጻጸም

፩· የፈቃድ ወረቀት የተሰጣቸው የማምረቻ መጋዘኖች በሮች በጉምሩክ እና በአምራቹ የጋራ ቁልፍ የሚቆለፉ ይሆናሉ።

*12. The Voucher*

1) The Customs Authority shall, on the basis of the export plan sent to it from the Ministry of Trade and Industry, determine the amount of voucher to be issued and notify same to the Ministry of Finance.

2) The Ministry of Finance shall, upon the request submitted by the Customs Authority, issue vouchers that will be used by the beneficiaries of the Voucher Scheme as deposit for taxes and duties payable on raw materials they import.

3) Vouchers issued in accordance with Sub-Article (1) above shall:

(a) have monetary value;

(b) be not-transferable to third parties;

(c) be denominated in Birr 100, Birr 50, Birr 10, Birr 5 and Birr 1 notes to facilitate their use as deposit.

## *Section 3*

## *Bonded Manufacturing Warehouse*

*13. Beneficiaries of the Scheme*

Beneficiaries of the Bonded Manufacturing Warehouse Scheme are producers wholly engaged in exporting their products who are not eligible to use the Voucher Scheme and who have license that enables them to operate such Warehouse.

*14. Condtions to be Fulfilled In order to become Beneficiary of the Bonded Manufacturing Scheme*

Persons that can be beneficiaries of the Bonded Manufacturing Warehouse Scheme are persons who have fulfilled the following conditions:

1) have manufacturing license;

2) having warehouse that has fully complied with all requirements provided for by Customs laws and regulations;

3) that have paid allowances to the Customs officials assigned in the warehouse and license fees as determined by law;

4) present evidence showing that they have insured the warehouse;

5) that can provide to the Customs Authority their annual export plan showing the type, quantity and value of the products they intend to export during the year, and the raw materials they import to use in such products;

6) submit input-output coefficient;

7) In addition to input and output coefficient submit a memorandum showing the amount of raw material wasted in the course of production process, the amount and type of by-product to be supplied to a foreign or local market, the input used out of the raw-material imported in the production of the by-product in percentage, during the execution of the annual production plan.

*15. Procedures for the Application of Bonded Manufacturing Warehouse Scheme*

1) The customs official and the exporter shall jointly lock the licensed warehouse.

፪· አምራቹ ከውጭ አገር ለሚያስመጣቸው ጥሬ ዕቃዎች የተላላፊ ዕቃ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት በመድረሻ የጉምሩክ ወደብ ፈፅሞ ጥሬ ዕቃዎቹ በቀጥታ ወደመጋዘኑ ከተላለፉ በኋላ፣ አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት በመጋዘኑ እየተፈጸመ ዕቃዎቹ ወደ መጋዘን ይገባሉ።

፫· ለምርት ተግባር የሚያስፈልገው ጥሬ ዕቃ በየጊዜው የጉምሩክ ሹም ባለበት እየተመዘገበ ወጪ ይደረጋል።

፬· የተመረተው ምርት ወደመጋዘን ተመዝግቦ ከገባ በኋላ የጉምሩክ የወጪ ዕቃ ሥነ ሥርዓት ተፈፅሞበት ወደ ውጭ አገር ይላካል።

፭· ጥሬ ዕቃው ወደመጋዘን ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ምርት ተመርቶበት ምርቱ ለውጭ ገበያ ካልተላከ አምራቹ በጥሬ ዕቃዎቹ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ ከነወለዱ እንዲከፍል ይደረጋል።

፮· በማምረቻ መጋዘኖቹ ሥርዓት አማካኝነት ከቀረጥ ነፃ በገቡ ጥሬ ዕቃዎች የተመረቱ ምርቶች በአገር ውስጥ ገበያ ሲሸጡ ሊከፈል የሚገባውን የሽያጭና ኤክሳይዝ ታክስ መሰብሰብ እንዲቻል የጉምሩክ ባለሥልጣን አስፈላጊ መረጃዎችን ለአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ይልካል።

፯· አምራቹ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የመላክ ንግድ ሥራውን ያቋረጠ እንደሆነ የጉምሩክ ባለሥልጣንን በማስፈቀድ ቀረጥና ታክሱን ከነወለዱ ከፍሎ ጥሬ ዕቃውን እና ምርቱን በአገር ውስጥ ገበያ ለመሸጥ ይችላል።

## ክፍል ፬

## አ ጠ ቃ ላ ይ

### ፲፮· የግብአት ምርት ጥመርታ

፩· የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የግብአት ምርት ጥመርታ ያዘጋጃል።

፪· ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ሥራ ላይ እስከሚውል ድረስ ላኪዎች ወይም አምራቾች የሚያቀርቡት የግብአት ምርት ጥመርታ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እየታየ በሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል።

### ፲፯· በምርት ሂደት ውስጥ ስለሚባክን ጥሬ ዕቃ

ለወጪ ንግድ ዕቃዎች ማምረቻ የዋለው ጥሬ ዕቃ መጠን በሚሰላበት ጊዜ በምርት ሂደት ውስጥ የባከነው ወይም የተበላሸው ጥሬ ዕቃ ግምት ውስጥ እንዲገባ ይደረጋል።

### ፲፰· የጉምሩክ ባለሥልጣን ተግባርና ኃላፊነት

፩· በዚህ አዋጅ በተቋቋመው የማምረቻ መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚ የሚሆኑ ሰዎች ወይም ድርጅቶች ሊከተሉት ስለሚገባ አፈጻጸም መመሪያ ያወጣል።

፪· በቂ ምክንያት ሲያገኝ የተመላሽ ቀረጥ እና የማምረቻ መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚ ለሚሆኑ ሰዎች እና ድርጅቶች የተሰጠው የጊዜ ገደብ ለተጨማሪ አንድ ዓመት እንዲራዘም ሊፈቅድ ይችላል።

### ፲፱· መመሪያዎች

የገንዘብ ሚኒስትሩ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚረዱ መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን ተሰጥቶታል።

2) The Exporter who imports raw materials shall complete transit formalities at the port of arrival and the raw materials shall directly be transferred to the warehouse. All necessary Customs formalities shall be completed at the Warehouse.

3) The raw material to be used for production must be removed in the presence of the Customs official.

4) The product shall be registered and transferred to the warehouse and shall be exported after all Customs export formalities have been completed.

5) Unless the raw materials tranferred into the warehouse are fully utilized and unless the products are exported within one year from the date of transfer to the warehouse, the exporter shall be made to pay the taxes and duties together with the interest thereon.

6) If products manufactured by the use of the raw-materials imported free of duty through the Bonded Manufacturing warehouse Scheme are sold locally, the Customs Authority shall transfer all required documents and information to the Inland Revenue Authority so that the Sales and Excise tax due thereon may be collected.

7) If, because of events beyond his control the producer has terminated his export activity, he shall, after securing the consent of the Customs Authority, sell the raw materials and the products locally upon payment of duties and taxes together with the interest thereon.

## Section 4

## *General*

### 16. *Input-Output Coefficient*

1) The Ministry of Trade and Industry shall develop the input–out put Coefficient within one year from the date of entry into force of this Proclamation.

2) Until the input–output coefficient is developed in accordance with the provisions of Sub-Article (1) above, the input, output coefficient developed by the exporters or producers shall be reviewed by the Ministry of Trade and Industry and be put into use.

### 17. *Raw Materials Wasted in the Process of Production*

When calculating the raw material used in the production of export commodities, the wastage and scrap of raw material shall be taken into account.

### 18. *Duties and Responsibilities of the Customs Authority*

1) Issue directives regarding the procedures to be followed by persons and organizations that are beneficiaries of the Bonded Manufacturing Warehouse Scheme established under this Proclamation.

2) Allow, for good cause, the extension of the period of limitations provided for in this Proclamation, for persons and organizations who are beneficiaries of the Duty Drawback and Bonded Manufacturing Warehouse Schemes for a period not exceeding one year.

### 19. *Directives*

The Minister of Finance is hereby empowered to issue directives for the proper implementation of this Proclamation.

## ፳. የወንጀል ቅጣቶች

፩. በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የበለጠ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ቀረጥ ከፋይ ቀረጥ ላለመ ክፈል ወይም አሳንሶ እንዲከፍል ለማድረግ ስለአመ ራረቱ፣ ስለሸቀጡ ዋጋ ፣ ሀሰተኛ መግለጫ የሰጠ፣ ትክክለኛ ያልሆኑ የሂሣብ መዛግብትንና ደጋፊ ሰነዶችን ያቀረበ፣ ወይም አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን እንዲያቀርብ ሲጠየቅ ፈቃደኛ ያልሆነ ፣ ወይም የደበቀ፣ አግባብ ያላቸውን የመንግሥት አካላት ሥራ በማናቸውም ድርጊት ያደናቀፈ ወይም ለማደናቀፍ የሞከረ ጥፋተኛ ሆኖ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥበት፤

ሀ) ጥፋቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈጸመ ሲሆን አምስት ዓመት የእሥራት ቅጣትና ብር ፳፭ሺ ይቀጣል።

ለ) ጥፋቱ ለሁለተኛ ጊዜ ሲሆን የአሥር ዓመት እሥራትና ብር ፶ሺ ይቀጣል።

ሐ) ጥፋቱ ለሦስተኛ ጊዜ የተፈጸመ ሲሆን የአሥራ አምስት ዓመት እሥራትና እና ብር ፸፭ሺ ተቀጥቶ የቀረጥ ማበረታቻ መብቱ ይሠረዛል።

፪. በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት በቫውቸር ሥርዓት ወይም በማምረቻ መጋዘኖች ሥርዓት አማካኝነት ወደአገር ያስገባውን ጥሬ ዕቃ የሸጠ ፣ ወይም በዚህ ጥሬ ዕቃ ያመረተውን ምርት በአገር ውስጥ ገበያ ላይ ሸጦ ተገቢውን ቀረጥና ታክስ ከነወለዱ ያልከፈለ ፣ ጥፋተኛ ሆኖ በፍርድ ሲረጋገጥበት በአሥራ አምስት ዓመት እሥራትና በብር ፸፭ሺ መቀጫ ይቀጣል።

፫. ይህንን አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት የሚወጡ ደንቦ ችንና መመሪያዎችን አፈጻጸም በማናቸውም ሁኔታ ያደናቀፈ ወይም ለማደናቀፍ የሞከረ ሰው ጥፋቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ይቀጣል።

## ፳፩. የተሻሩ እና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

፩. ለወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር ፷፱/፲፱፻፹፭ በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

፪. ይህን አዋጅ የሚቃረን ወይም በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን የሚመለከት ማናቸውም ሕግ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

## ፳፪. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ለውጭ ገበያ ለሚውሉ ሸቀጦች ማምረቻ እንዲያገለግሉ መያዣ ተከፍሎባቸው ወደአገር የገቡ ጥሬ ዕቃዎች ቀደም ሲል በሥራ ላይ በነበሩ ሕጎች መሠረት ፍጻሜ ያገኛሉ።

## ፳፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

## *20. Offences*

1) Unless the relevant provisions of the Penal Code impose greater penalty, any Duty-payer who, with the intention of evading or under paying the duty, makes false declaration concerning his production activity, prices, or submit incorrect books of accounts and supporting documents or refuse to supply, or conceals information necessary, or in any way, obstructs or attempts to obstruct the work of the Authority shall upon conviction by the court be punishable:
   (a) with five year imprisonment and birr 25,000 (twenty five thousand Birr) fine, if the offense is committed for the first time;
   (b) with ten years imprisonment and birr 50,000 (fifty thousand Birr) fine, if the offense is committed for the second time;
   (c) in addition to fifteen years imprisonment and birr 75,000 (seventy five thousand Birr) fine, his incentive privilege shall be withdrawn, if the offense is committed for the third time.
2) Any person who sold raw materials imported under the Voucher or Bonded Manufacturing Warehouse Schemes, or sold commodities it produced with raw materials imported under such schemes locally without payment of taxes and duties and interest due thereon shall, upon conviction by the court, be punishable with 15 years imprisonment and a fine of Birr 75,000.00.
3) Any person who, in any way, obstructs or attempts to obstruct the implementation of this Proclamation or regulations and directives to be issued hereunder, shall upon conviction by the court, be punishable in accordance with the Penal code.

## *21. Repeals and Inapplicable Laws.*

1) Export Trade Duty Incentive Scheme Establishing Proclamation No. 69/1993 is hereby repealed.
2) Any law inconsistent with this Proclamation shall be inapplicable with regard to matters provided for in this Proclamation.

## *22. Transitory Provisions*

Raw materials imported on deposit or guarantee prior to the coming into force of this Proclamation for the production of export commodities shall be finalized in accordance with legislations that were in force.

## *23. Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 5th day of July, 2001.

*Done at Addis Ababa, this 5th day of July, 2001.*

*NEGASO GIDADA (DR.)*

*PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE